# ከኢትዮጵያ እስከ ሳውዲ አረቢያ በተሰኘ መርሃ መፌክር ሥር

# <u>የተቃውሞ ሰልፍ በኑርንበርግ ከተማ ጀርመን ተካሄደ !!</u>

ይህ በአለም አቀፍ ደረጃ በሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን እየተካሄደ ከሚገኘው የተቃውሞ እንቅስቃሴ አካል የሆነውና በኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴና በኢሕአፓ ወክንድ በእለተ ቅዳሜ ሕዳር 14 ቀን 2006 ዓ.ም. (Nov. 23 ቀን 2013) „ከኢትዮጵያ እስከ ሳውዲ አረቢያ" በተሰኘ መርሃ መፍከር የተዘጋጀ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ በርከታ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቅቋል። የሰልፉ ዋና አላማም በዜጎቻችን ላይ የሚደርሰውን በደልና ጭቆና፤ መከራና ሥቃይ ድምፅ ለተነፈጋቸውና ድምጽ አላባ ሆነው በሀገራችን በወያኔ አገዛዝ ሥር፡ በሳውዲ አረቢያና በጠቅላላ በሌሎች ሀገር ጭምር ያለ ፍላጎት ተሰደው በተሻለ ኑሮ ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ ባጋጠማቸው በበደልና ብዝበዛ እየተሰቃዩ ለሚገኙት ወገን ዜጎቻችን ድምፅ በመሆን በጀርመን ሀገር ለሚኖረው ሕዝብና ለአለም አቀፍ ሰላም ወዳድ ማህበርሰብ በማሰማት የሚታደጉበት ሁኔታም እንዲፈጠር ነው።

በሰላማዊ ሰልፉ የወያኔን አገዛዝ የሚያጋልጡና እንዲሁም በሳውዲ አረቢያ መንግሥት አማካኝነት በዜጎቻችን ላይ የተደረገውንና እየተደረገ ያለውን ኢሰብአዊ እርምጃ የሚያጋልጥጡ፤

- ብሔራዊ ውርደትና ስደት ያብቃ!
- ሀገር ማዳን የዜግነት ጉዳይ ነው!
- ወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ነው!
- ወያኔ ሕዝብና ሀገር ገዳይ ነው!
- በሳውዲ አረቢያ ለደረሰው እልቂት ተጠያቂው ወያኔ ነው!
- የሳውዲ ንጉስ በዜጎቻችን ላይ ላደረሰው ግድያና አፈና በአለም ቀፍ ፍርድ ቤት ይጠየቅ!

የሚሉና እንዲሁም በእንግሊዝኛና በጀርመንኛ የተፃፉ መፈክሮች በሰላማዊ ሰልፈኞቹ ተስተጋብተዋል።

በሰላማዊ ሰልፉ የትዕይንት ሂደት በኢሕአፓ፤ በየኢሕአፓ ወጣት ክንፍ እንዲሁም በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴና አንድ

በጀርመንኛ የዜጎቻችንን ስቃይ የሚያብራሩ መግለጫዎች ለጀርመን ዜጎችና ለሰላማዊ ሰልፉ ተካፋዮች በስፋት ተበትነዋል።

በመጨረሻም በሰልፉ ማሳረጊያ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ያወጣው መግለጫ በወጣት ሴት መቅደስ ለተሰብሳቢው ተነቦ በመጨረሻም በእለቱ ኢሕአፓ የተመሰረተበት ቀን በአሜሪካ በዋሽንግተን ዲሲ የሚከበርና ባለፉት 41 አመታት በፅናት እየታገለ ያለ ድርጅት መሆኑ ተገልጿል። ከዚሁ ጋር በማያያዝም ዋናው ለችግራችን ምንጭ ዋና ተጠያቂው ሌላ ሳይሆን የወያኔ አገዛዝና ሥርአት መሆኑ አፅንዖት በተሞላበት መልክ ተገልጾ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሕዝባችንን ለመታደግ የግዴታ መደራጀትና መታገል እንደሚገባና ለዚህ ስኬታማነትም ሁሉም በያለበት የበኩሉን አስተዋፅዖ እንዲያበረክት ሀገራዊ ጥሪ በማድረግ የቀኑ ትዕይንት ተገባዷል።

23.11.2013